የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን

# የትምባሆ ምርት አስመጪ፣ ላኪና አከፋፋይ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መስፈርቶች

መስከረም 2004

**ማውጫ**

መግቢያ ........ 3
ክፍል አንድ: ጠቅላላ ........ 4
1. ዓላማዎች ........ 4
2. የተፈፃሚነት ወሰን ........ 4
ክፍል ሁለት ........ 5
3. የብቃት ማረጋገጫ አስፈላጊነት ........ 5
4. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይዘት ........ 6
5. የህንፃው ዲዛይንና የአካባቢ ሁኔታ ........ 6
6. አስፈላጊ ግብዓቶች ........ 7
7. የሰው ኃይል ሞያና ስልጠና ሁኔታ ........ 8

# መግቢያ

የትምባሆ ዝግጅቶች ስርጭትና አጠቃቀም በተገቢው ሁኔታ ካልተካሄደ በህዝቡ ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል፡፡ የትምባሆ ዝግጅት አያያዝ፣ አከማቻቸትና አጓጓዝ በተገቢው ሁኔታ ካልተካሄደ እንዲሁም ጥራቱንና ደህንነቱን ጠብቆ ለአጫሾቹ ካልደረሰ በአጫሾቹ ላይ እና ሌሎች ለትምባሆ ጭስ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ሌላ ተጨማሪ ጉዳት ሊያደረስ ይችላል፡፡ በመሆኑም ወደ ተጠቃሚው እስኪደርስ ድረስና ከደረሰ በኃላም ተገቢውን ጥንቃቄ ሊደረግለት ስለሚገባ፡፡

የትምባሆ ምርቶችን ማጠቀም በጤና ላይ የሚያደርሱትን ከፍተኛ የሆነ የጤና ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት የትምባሆ ምርቶችን ማጠቀም እንዳይበረታታ ለማድረግ እና የትምባሆ ምርቶችን ተጠቃሚዎችን ለመቀነስ አስፈላጊ በመሆኑ፡፡ እንዲሁም የትምባሆ ምርቶችን የማስመጣት፣የመላክ እና በጅምላ የመሸጥ ብሎም አጠቃላይ ስርጭቱን በመቆጣጠር ከሚያደርሰው የጤና፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ከባቢያዊ ተፅዕኖ አኳያ እንዳይበረታታ ለማድረግ በማስፈለጉ

በመሆኑም የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በተሰጠው ኃላፊነት ማሰረት የትምባሆ ምርቶችን ቁጥጥር፣ ሕገወጥ ዝወውርና አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት ባለሥልጣኑ መመሪያ አውጥቶ በተግባር እስኪያውል ድረስ የሚከተለውን የብቃት ማረጋገጫ ማሰፈርቶችን አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ፡ ጠቅላላ

## 1. ዓላማዎች

በሀገራችን በትምባሆ ምርት አስመጪ፤ ላኪና ጅምላ አከፋፋ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩና የሚሰማሩ ድርጅቶች አስፈላጊውን ማስፈርት እንዲያሟሉ በማድረግ የብቃት ማረጋገጫ ለማስጠት ነው፡፡

## 2. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ማስፈርት በሁሉም የትምባሆና ትምባሆ ምርት ወጤቶች ላይ በማስመጣት፣ መላክና ማከፋፈልን የተሰማሩና የሚሰማሩ የንግድ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

### 3.የብቃት ማረጋገጫ አስፈላጊነት

1. ማንኛውም ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ሳያገኝ የትምህርት ማስመጣት፣ ማከና ማከፋፈል አይችልም፡፡
2. የብቃት ማረጋገጫምስክር ወረቀት ለማግኘት ማመልከቻ የሚቀርብ የትምህርት ዝግጅት አስመጪ፣ ላኪና አከፋፋይ ድርጅት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማሟላት አለበት፡፡

   ሀ/ አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ መፈፀም

   ለ/ የአመልካቹ ሙሉ ስምና ዜግነት

   ሐ/ የድርጅቱ ስምና አድራሻ

   መ/ ሊሰራ ስለታሰበው የትምህርት ንግድ አይነት፡፡

   ሠ/ ሌሎች ባለስልጣኑ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነባቸውን መረጃዎች ማካተት አለበት፣

   ረ/ የተሟላ ማመልከቻ ካልቀረበ በድጋሚ ተስተካክሎ ሊቀርብ ይችላል፡፡
3. ማመልከቻዉ የተሟላ ከሆነ ከሁለት እስከ ሦ**ስት አባላት ባሉት** የተቆጣጣሪ ቡድን ለመጀመሪያ ጊዜ ያለክፍያ ይታያል፡፡
4. ድርጅቱ በቅድመፈቃድ ቁጥጥር ወቅት ማሟላት ያለበትን እንዲያሟላ ተነግሮት ካላሟላ ተገቢውን ክፍያ ከፍሎ እስከ ሁለት ጊዜ ሊታይለት ይችላል፡፡

## 4.የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይዘት

ማንኛውም በዚህ መስፈርት መሰረት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫምስክር ወረቀት የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡፡

1. የድርጅቱ ባለቤት ስም፣
2. የድርጅቱን ስምና አድራሻ፣
3. የድርጅቱን አይነት፣
4. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሠጠበትና የሚታደስበትን ቀን
5. የሰጠው አካል ሙሉ ስም፡ ፊርማና የባለሥልጣኑ ማህተም፣
6. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር፣
7. የቴክኒክ ኃላፊ ስምና ሙያ
8. በፊታዱላይ የሚሰፍሩ ዝርዝር ሁኔታዎች ወይምማሳሰቢያዎች፡፡

### ክፍል ሶስት

### የህንፃው ዲዛይንና የአካባቢ ሁኔታ፣ አስፈላጊ ግብአትና የሰው ኃይል

## 5. የህንፃው ዲዛይንና የአካባቢ ሁኔታ

1. የትምባሆ ዝግጅቶች ንግድ ድርጅት የሚቋቋምበት አካባቢ ቀጥሎየተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፡፡
   - ሀ/ የመሰረተ ልማት አውታሮች የተሟሉለት መሆን አለበት
   - ለ/ ከሰውመኖሪያ ቤት የተለየ ሆኖ ከሌላ ህንፃ ጋር ወስጥ ለወስጥ የማይገናኝ
   - ሐ/ ከነብሳት መራብያ፣ ቆሻሻ መጣያ፣ መጥፎ ሽታ፣ ረግራጋማቦታ፣ ከጎርፍ፣ ኬሚካልና ጭስ ከሚጠቁባቸውቦታዎች እንዲሁም በሰውጤና ደህንነት ላይ አደጋ ለሚያስከትሉ ነገሮች ተጋላጭ ያልሆነ፣
2. የትምባሆ ዝግጅት ንግድ ድርጅት ቢያንስ የማከማቻ እና የማከፋፈያ ክፍሎች በአንድ ቦታ ሊኖሩት ይገባል፡፡
3. የማከማቻ እና የማከፋፈያ ክፍሎች ዲዛይንና አሰራር የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡፡
   - ሀ/ ግድግዳዉ ከድንጋይ ወይም ከብሎኬት ወይም ከሸክላ የተሰራ ሆኖ በሊሾ ሴሜንቶ የተለሰነና ልሙጥ እንዲሁም ሊታጠብ በሚችል ቀለም የተቀባ፣
   - ለ/ ኮረኒሱ ከኮንክሪት ወይም ችቡድ የተሰራ መሆን አለበት፡፡ ከጨፍቅ ወይምከማዳበሪያ ወይም ቆርቆሮ የተሰራ መሆን የለበትም፡
   - ሐ/ ወለሉ ከሲሚንቶ ወይምሴራሚክ የተሰራ ሆኖ ሊታጠብ የሚችልና ቆሻሻ የማይይዝ

መ/ ክፍሎቹ በቂ ብርሃን ሊያስገቡ የሚችሉ፣ በቂ የአየር ዝወውር ያላቸውና ቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃን የሚያስገባ ሊሆን ይገባል

ሠ/ የተበላሹ ወይም የማጠቀሚያ ጊዜቸው ያለፈባቸው ወይም ከገበያ የሚወጡ የትምባሆ ዝግጅቶች ተለይተዉ የሚቀመጡበት የተለየ ማቆያ ቦታ ወይም ክፍል ያለው

ረ/ የትምባሆ ዝግጅቶች የሚከማቹት ከሜሬት ቢያንስ 20 ሴ.ሜ ከፍ ብለው፣ ከግድግዳው ቢያንስ 20 ሴሜ ርቀው፣ ከጣሪያዉ ቢያንስ 30 ሳ.ሜ ዝቅ ብለው እንዲሁም በማ/ከላቸው ቢያንስ አንድ ሜትር ተራረቀው በተቀመጡ መደርደሪያዎች መሆን አለበት አለባቸው

ሰ/. የትምባሆ ዝግጅቶች ያለ መደርደሪያ ማከማቸት ሲፈለግ ከሜሬት ቢያንስ 20 ሴ.ሜ ከፍ ብለወና ከግድግዳው ቢያንስ 20 ሴሜ ርቀው እንዲሁም በማ/ከላቸው ቢያንስ አንድ ሜትር ተራረቀው በተቀመጡ ፓሌቶች መሆን አለበት፡፡

ሸ/. ማከማቻው ክፍል ስፋት እንደሚያከማቸው የትምባሆ መጠን የፓሌቶቹ ወይም መደርደሪያዎች ብዛትና ስፋት ታይቶ ሊሰፋ ይችላል፡፡

## 6.አስፈላጊ ግብዓቶች

ማንኛወም የትምባሆ ንግድ ድርጅት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ግብአቶች ማሟላት አለበት፡፡

1. በአንቀፅ አምስት ንዑስ አንቀፅ (ረ) እና (ሰ) ያለው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በቂ መደርደሪያዎችና ፓሌቶች ሊኖሩት ይገባል
2. የትምባሆ ዝግጅት ለእይታ የሚቀርቡበትና የሚቀመጥበት ማዙሪያል ለቀጥተኛ የፀሀይ ብርሃን የሚያጋልጥ ሁኖ በቀላሉ ሊፀዳ የሚችል፣ ከዝገት የፀዳ እና በምርቱ ላይ ብክለት የሚያመጡ መሆን አለባቸው
3. በማከማቻ ክፍሎች እንደአስፈላጊነቱ የአየር ኮንዲሽነር (AC) ወይም ቬንትሌተር ሊኖረው ይገባል
4. የእርጥበት ማከኒያና የሚንጠለጠል የግድግዳ የሙቀት ማለኪያ ማርያዎች መኖር አለበት
5. የእሳት አደጋ በከላከያ መሳርያ ሊኖረው ይገባል
6. የመጀመሪያ የህክምና ዕርዳታ መስጫ ማሳርያ ቢኖረው ይመረጣል
7. የሽያጭ ሰራተኞቹ በሰራ ጊዜ የሚለብሱበት የደንብ ልብስ መኖር አለበት
8. ድርጅቱ ከስርጭት ጋር ተያያዝነት ያላቸው መረጃዎች ለመያዝ የሚያስችል ስርዓት ሊኖረው ይገባል

## 7.የሰው ኃይል ሞያና ስልጠና ሁኔታ

1. ድርጅቱ በቴክኒክ ኃላፊነት የሚመራው ባለሞያ ቢያንስ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ 10ኛ ክፍል ወይም በነባሩ የትምህርት ፖሊሲ12ኛ ክፍል ያጠናቀቀና ዕድሜው ከ 18 ዓመት በላይ መሆን አለበት
2. ማንኛወም በትምባሆ ዝግጅቶች ንግድ ስራ የሚያሰማራቸው ሰራተኞች ስለ ትምባሆ ዝግጅቶች አያያዝ፣ አከማቻቸት እንዲሁም አጓጓዝ እና ሌሎች በጉዳዩ ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች ማሰረታዊ እወቀት ሊኖረው ይገባል

## ዕዝሎች

## የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለ ስልጣን
## የትምባሆ ምርት ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት
## <u>ማጠየቂያ ቅጽ</u>

1 **የአመልካች ሙሉ ስም** ______________________________

2 **የአመልካች የመኖሪያ አድራሻ**

ክልል____________ዞን/ክ/ከተማ______________ወረዳ______________ከተማ___________ቀበሌ______________
___ስ/ቁ______________ ሞ/ቁ_______________ኢሜል____________________________

3 **አመልካቹ/ቿ በድርጅቱ የሚኖረዉ/ራት ኃላፊነት /መረጃ ይያያዝ/፣** ______________________________

4 የንግድ **ድርጅቱ ባለቤትነት (የግል፣ ኃ/የ/ማህበር፣ የአክሲዮን፣** የመንግስት፣ መያድ/

5 የድርጅቱ ባለቤት ሙሉ ስም____________________________________________

6 የንግድ **ድርጅት ዓይነት** ____________________________________________

7 የንግድ **ድርጅቱ አድራሻ፣**

ክልል ______________ ዞን/ክ/ከተማ______________ወረዳ_________________ከተማ_______________
ቀበሌ________________________ስ/ቁ__________________ሞ/ቁ_______________ኢሜል______________
ቦታው ልዩ ማጠሪያ ________________________________________________________________________

9 የድርጅቱን ቴክኒካል ባለሙያ

9.1 ሙሉ ስም____________________________________
9.2 የትምህርት ደረጃ ________________________________
9.3 ሙያ ዓይነት ____________________________________
9.4 ዕድሜ____________________________________
(የባለሞያው የወል ስምምነትና የትምህርት ማስረጃ ይያያዝ)

11. እኔ ________________________________ የተባልኩኝ በብቃት ማረጋገጫ ማስፈርቱ ላይ የተቀመጡትን ድርጅታዊና ሙያዊ ማስፈርቶች ስላሟላሁኝ ድርጅቴን ታይቶ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ፡፡

ፊርማ ________________________________

ቀን ____________________________

የድርጅቱ ማህተም

---

**12. ለአፊስ ስራ ብቻ የሚያገለግል**

12.1 የማመልከቻው ተቀባይ ሰራተኛ ስም ______________________ፊርማ ___________
12.2 ማመልከቻው የተቀበለበት ቀን ________________ሰዓት_______________________
12.3 የቀጠሮ ቀን ____________________ሰዓት________________